# ***<u>የአባይ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ከየት ወዴት?</u>***

ኢትዮጵያ ከማንኛዉም አባይ ተፋሰስ አገራት በላይ የአባይ ወንዝን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በጋራ ለመጠቀም ለረጅም አመታት ዲፕሎማሲያዊ ትግል ስታደርግ ቆይታለች። ይህ የረጅም አመታት ዲፕሎማሲያዊ ትግል “ፍሬያማ ወይስ ፍሬ አልባ?” ብሎ መጠየቅና ተንትኖ ማየት አስፈላጊ ነዉ። ዲፕሎማሲያዊ ትግሉን ክፍል በክፍል አስቀምጠን እንመልከት።

***ኢትዮጵያ ፍትሃዊና የጋራ ተጠቃሚነት አቋሟን የማስረዳት ዲፕሎማሲ***

ኢትዮጵያ የአባይ ዉሃ 86% አመንጪ ሆና ሳለች ለሺህ አመታት ከብት ከማጠጣትና በገንቦ ከመቅዳት የዘለለ ጥቅም አላገኘችም። “በኢትዮጵያ ህልዉና ላይ አደጋ የሚጋርጥ ጠላት ድህነትን ከዜጎቿ ጨንቃ አሸቀንጥሮ ለመጣል የአባይ ወንዝን ፊትሃዊ በሆነ መንገድ ለጋራ ጥቅም ማዋል” የሚለዉን የማይነቃነቅና የማያወላዳ አቋሟን ለተፋሰሱ አገራትና ለዓለም ሁሉ በማስረዳት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ዉጤት ማግኘት ችላለች።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች በአንድ ቀን ዉስጥ በአንድ ስብሰባ አዳራሽ ከ 21 ሰዓታት በላይ  ቁርስ፣ ምሳና እራት በድርድር ወንበር ላይ በልተዉ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበርና የኢትዮጵያን አቋም ለሌሎች ተፋሰሱ አገራት ለማስረዳት ታግሏል። በአሮጌዉ የግብጽ ዉሃ ፖለትካ ሪዮተ-ዓለማዊ ጡንቻ ማስፈራራት፣ማዳከምና መበታተን የተነሳ በታሪክ በዉሃ ጉዳይ ላይ ተባብሮና ተስማምቶ የማያዉቁ የታችኛዉ ተፋሰስ አገራት ሱዳንንም ጨምሮ ከዲፕሎማሲያዊ ትግሉ የተነሳ አሁን ተግባብቶና ተደጋግፎ ለጋራ ተጠቃሚነት አብሮ ለመስራት ቃል የሚገቡበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

***የተሳሳተ የግብጽ አቋምን ለሌሎች የማስረዳትና ለዓለም የማጋለጥ ዲፕሎማሲ***

ጠብታ ዉሃ አስተዋጽኦ የማታበረክት ግብጽ “ጠብታ ዉሃ በግብጻዊያን ጠብታ ደም ይቀየራል”  በሚል ገታራ አቋምና በቅኝ ገዥዋ እንግሊዝ አማካይነት እ.ኤ.አ. በ1902፣1929 እና 1959 የተፈረሙትን «አግላይ» ስምምነቶችን በማጣቀስ «በናይል ወንዝ የመጠቀም መብቱን በጥቂቱ ለሱዳን የማካፈል ግዴታ አለብኝ፣ ውኃው የግብጽ ነው፤» የሚለዉን የተሳሳተ የግብጽን አቋም በዲፕሎማሲያዊ መንገድና በሰከነ አካሄድ ለመለወጥ ለኢትዮጵያ እጅግ በጣም ፈታኝ አጀንዳ ቢሆንም የግብጽ አቋምና አስተሳሰብ የተሳሳተ እንደሆነ ለሌሎች ተፋሰሱ አገራት በማስረዳት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያ አቋም ጎን በማሰለፍ በታሪክ ተገኝቶ የማያዉቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ለመጎናጸፍ ችላለች።  የተሳሳቱ የግብጽ ፖለትከኞች የኢተዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ የማስተባበርና ማቀናጀት ስራ ኢትዮጵያ በግብጽ ላይ ሌሎችን እያሳመጸችና እያበረች እንደሆነ በማሰብ በተለያዩ ግዜያት በማጣጣልና እንደ አፍራሽ ተግባርም በመፈረጅ ቆይቷል። ቢሆንም የማታ የማታ ዲፕሎማሲያዊ ድሉ ለኢተዮጵያና የጋራ ተጠቃምነት መርህ ደጋፊዎች መሆኑ አልቀረም።

*በአባይ ጉዳይ ላይ ሌሎች አገሮችን የማስተባበርና አዲስ ፍትሃዊና የጋራ ዉሃ አጠቃቀም ስምምነት የመፈረም ዲፕሎማሲ*

ኢትዮጵያ ከረጅም አመታት ዲፕሎማሲያዊ ትግልና ሌሎችን የተፋሰሱን አገራት ከማስተባበር ድካም በኋላ በአባይ ዉሃ አጠቃቀም ዙሪያ አዲስ የውኃ ፍትሃዊና የጋራ አጠቃቀም ስምምነት (CFA: comprehensive framework agreement) በዩጋንዳ ኢንቴቤ በበርካታ ተፋሰሱ አገራት እንዲፈረም በማድረግ ወደር የማይገኝለት የዲፕሎማሲ ዉጤት አስመዘግባለች።

የስምምነቱ ድርድር ሂደት አሳታፊ፣ ረጅም ጊዜ፣ ትዕግሥትና ጥበብ የጠየቀ ነበር። ስምምነቱ ናይል የሁሉም ተጋሪ ሀገሮች የጋራ ሀብት መሆኑን መነሻ ያደረገ፤ከዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችና ሕግጋት ጋር የሚጣጣም፤ በሁሉም ተጋሪ ሀገሮቹ የተቀረጸ፤ማንንም ያላገለለ፤ፍትሐዊ ሥርዐት የሚዘረጋ እንድሆን ኢትዮጵያ ከማንም በላይ ጉልህ ሚና ተጫዉታለች። እንድሁም ይዘቱ የናይልን ተፋሰስን የውሃ አጠቃቀም ልማት፣ ጥበቃ፣ ፤እንክብካቤና አስተዳደር በተመለከተ በሀገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚወስንና ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ማዕቀፍ ሆኖ እንድፈረም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ዲፕሎማሲያዊ ትግል በማድረግ ለስምምነቱ ፍጻሜ መድረስ የበኩላቸዉን አስተዋጽዖ አበርክቷል።

*ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጀመርና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ*

የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ ከመጀመር ጋር ተያይዞ ከግብጽ ፖለትከኞችና ሚዲያ በኩል የሚደረጉ ዲፕሎማሲያዊና ኢ-ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን ለመመከትና ለመግታት የተደረጉ የኢትየጵያ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ፈርጀ ብዙና እልህ አስጨራሽ የነበሩና አሁንም ሳይበርዱ ሳይቀዘቅዙ የሚቀጥሉ ናቸዉ። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከተጀመረ በኋላ በግብጽ ፖለትከኞች በኩል ስሰነዘሩ የነበሩ አፍራሽና ጦር ቀስቃሽ ሁካታዎች እጅግ በጣም ብዙና ኢ-ዲፕሎማሲያዊ ነበሩ።

*ሱዳንን የማስረዳትና የማግባባት ዲፕሎማሲ*

በቅኝ ግዛት ዘመን 1959 እ.ኤ.አ. ሌሎች የናይል ተፋሰስ አገራትን በማግለል ሱዳንና ግብፅ በተፈራረሙት ስምምነት መሠረት ከናይል ውኃ 35% የመጠቀም መብት ለሱዳን ተሰጥቶ ነበር፡፡ ከዚህ ስምምነት ውጪ በውኃው ጉዳይ የሱዳንና የግብፅ ትብብር ለዘመናት የዘለቀና በጣም ጠንካራ የሚባል ነበር፡፡ በአባይ ወንዝ ጉዳይ ግብጽና ሱዳን የሚገናኙበትን በጠንካራ መሰረት ላይ የነበረዉን ግንኙነት አፍርሶ ሱዳንን መነጠል ከባድ ነበረ። ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር የተግባባችበትና ግድቡን የደገፈችበት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

1ኛ ኢትዮጵያ ባደረገችዉ ረጅም ግዜ ዲፕሎማሲያዊ ማስረዳትና ማግባባት ሱዳን የኢትዮጵያን አቋም እንድትደግፍ ማድረግ ተችሏል።

2ኛ ኢትዮጵያ በራሷ ተነሳሽነት ማንም ሳያስገድዳት ዓለማቀፍ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ተዋቅሮ በሱዳንና ግብጽ ላይ ግድቡ ጉልህ ጉዳት እንደማያደርስ በጥናት መረጋገጡ

3ኛ ግድቡ ለሱዳን፣ ግብጽና አጠቃላይ ለአፍሪካ እንድሁም ለመላዉ ዓለም ጥቅም እንደሚያስገኝ በመረዳቷ የኢትዮጵያን ግድብ እንድትደግፍ አድርጓታል።

4ኛ በኢትዮጵያና ሱዳን መካከል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ወይም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ግንኙነት እየተጠናከረ መሄዱ ሱዳን አቋሟን እንድትቀይር ተጽኖ አሳድሯል። (ስለ ኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎችን በሚቀጥለዉ ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን)

***የግብጽ ፖለትከኞች ሩጫና የሚዲያ ድንፋታ የመቀልበስ ዲፕሎማሲ***

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መሰረት ድንጋይ ከተቀመጠዉ ማግስት ጀምሮ የግብፅ ፖለትከኞችና ሚዲያ በግድቡ ላይ የከፈቱት አፍራሽ ዘመቻ ቀላል የማይባል ነዉ። በአረብ ፀደይ አብዮት ግዜ ከስልጣን በወረዱት ግብጽ ፕሬዚዳንት ሞሃመድ ሙርሲ ግዜ በቀጥታ ቴሌቭዥን ስርጭት ጭምር በኢትዮጵያ ላይ ጦር የማወጅ ሃሳብ ያቀረቡ ፖለትከኞችና ምሁራንም እንዳሉ ተመልክተናል። የግብጽ ፖለትከኞች ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉዳይን ዓለማቀፋዊ ይዘት እንድኖረዉና በአከባቢያዊ ፀጥታ ጉዳይ ላይ ተፈርጆ እንድታይ ለማድረግ የት የሌለ እንቅስቃሴ አድርጓል።

ከፈርኦኖች ዘመነ መንግስት ጀምሮ የግብፅ ፖለቲከኞች ለሺህ ዘመናት ከግብፅ የውኃ ድርሻ አንዲት ጠብታ እንኳን መቀነስ መዘዙ የከፋ እንደሚሆን ሲያስፈራሩ ኖረዋል፡፡ በአረብ ፀደይ አብዮት ስትናጥ በነበረችዉ የግብፅ አስተዳደር ውስጥ የመስኖ ሚኒስትር የነበሩ መሐመድ አብዱል ሙታሊብ፣ ባለፉት ወራት ዉስጥ “የግብጽን የውኃ ድርሻ መቀነስ ግብፅ ለማንም እንዲሻገር የማትፈቅደው ‘ቀይ መስመር ነዉ” እያሉ ሲገልጹ መቆየታቸዉ የሚታወስ ነዉ።

በሚዲያና ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ስለግድቡ ክፉ ከመናገር ባሻገር ወደተለያዩ ዓለም ክፍሎች በመሯሯጥ ግድቡን ለማስቆም ጥረት አድርጓል። ለምሳሌ ወደ ጣሊያን ፣ ራሺያ፣ ታንዜንያና ሌሎች በርካታ አገራት በመሄድ አቋማቸዉን አስረድቷል። ድጋፍም ለማግኘት ጥረት አድርጓል። የማያዋጣ አቋማቸዉን የተረዱ መንግስታት “ሂዱና ከኢትዮጵያ ጋር በድርድርና ዲፕሎማሲ ችግሩን ፍቱት” ብለዉ መልሷቸዋል።

የግብፅ ብሮድካስትና ፕሪንት ሚዲያዎች በግድቡ ላይ የሚያካሂዱት ዘመቻ እስከ አሁን ድረስም የቀጠለ ቢሆንም ትንሽ ትንሽ ትኩሳቱ እየበረደ መጥቷል። የተሳሳቱ ፖለትከኞች የሚያስተላልፉትን አፍራሽ መልዕክቶችን በቀጥታ ወደ ግብጽ ህዝብ በማዉረድና ስለግድቡ ሃሰት መረጃዎችን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በመዝራት የግብጹ ሚዲያ ከፍተኛ አሉታዊና አፍራሽ ተጽኖ አድርሷል፤ እያደረሰም ነዉ። እንድሁም ጡረታ የወጡ አክራሪ የጦር ጀነራሎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የግብጽ ሚዲያዉ የጦርነት ቅስቀሳ መልዕክቶችን ስያሰራጭ ቆይቷል።

ከአንዳንድ ግብፅ ምሁራን በኩል ከፖለቲከኞችና ሚዲያ ስህተት ፕሮፓጋንዳ ርቆና ተለይቶ ግድቡን የደገፉ ምሁራንም አልታጡም። ከነዚህም መካከል በአለክሳንደሪያ ዩኒቨርሲቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር ሲቪል ኢ/ር ዶ/ር ሃይተም ማምዱህ በየካቲት ወር 2006 ዓ.ም በናይል ቴሌቭዥን ቀጥታ ስርጭት ላይ ባደረጉት ቃለ ምልልስ ግድቡ ለግብፅ ተጨባጭ ጥቅም እንደሚያስገኝና ለኤሌክትርክ ሃይል ማመንጫ ብቻ የሚገነባ በመሆኑ የግብጽ ዉሃ መጠን እንደማይቀንስ የተናገረ ሲሆን የግብጽ ፖለትከኞች በጥናትና ምርምር መረጃ ላይ ያልተደገፈ አቋም በማራመዳቸዉ ትክክል አለመሆናቸዉንም ወቅሷል።

ሌላኛዉ የግብፅ ዉሃ ምሁር ሪቻርድ ቱትሌር ኢትዮጵያ የአባይን ዉሃ ለኤሌክትርክ ሃይል ማመንጫ ግድብ እስከተጠቀመች ድረስ የአባይ ዉሃ የሃይል ማመንጫ መዘዉሮችን ካንቀሳቀሰ በኋላ ያለምንም መቀነስ ከግድቡ ወጥቶ ወደ ግብጽ እንደሚደርስ መስክሯል።

**የኢትዮጵያ ግብረ መልስ ዲፕሎማሲ ለግብጽ ፖለትከኞችና ሚዲያ**

የግብፅን አፍራሽ ዲፕሎማሲያዊና ኢ-ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ መግለጫዎችን ሰጥተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የአውሮፓ አገራት አምባሳደሮችን ጠርተዉ ግድቡ በግብጽ ላይ ተጽኖ እንደማያደርስና ኢትዮጵያ በፍትሃዊና በጋራ አጠቃቀም ላይ እንደምታምን አስረድቷል።

በተለያዩ ግዜያት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በግብጽና ሱዳን ላይ ጉልህ ጉዳት እንደማያደርስ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ለተለያዩ አካላት አስረድቷል። ግብፅ ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ብትወስድ እንኳን የማሸነፍ ዕድል ስለሌላት በድርድሩ መሳተፍ ብቻ እንደሚያዋጣት ገልጸዋል፡፡ ወደ የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት ጉዳዩ ቢቀርብም ግብፅ ተሸናፊ ወገን እንደምትሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም መግለጻቸዉ አይዘነጋም፡፡

በምንም መንገድ ግድቡ እንደማይቋረጥ የውኃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዓለማየሁ ተገኑ በተደጋጋሚ ለግብፅ አቻቸው በዲፕሎማሲያዊ አካሄድ አሰረድቷል፡፡

የኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም በበኩሉ ሰፊ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ ትግል በማድረግ ለዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን አቋምና ግድቡ ግብጽን እንደማይጎዳ ማስረዳት ችሏል። የግብፅ እንቅስቃሴን በተመለከተም ዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዉጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሴዎች የዘወትር ተግባራቸዉ አድርገዉ ባገኙት አጋጣም ሁሉ የኢትዮጵያን አቋም እንድያስረዱና ግድቡ ግብጽን እንደማይጎዳ እንድያብራሩ በማድረግ ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ዉጤት ማስገኘት ችሏል፡፡ እንድሁም በተለያዩ ግዜያት በዓለም ዓቀፍና አገር ዓቀፍ ሚዲያዎች የተለያዩ አስረጂ ጽሁፎችን በማዉጣት፣ ቃለመጠይቆችንና መግለጫዎችን በመስጠት ኢትዮጵያ በፍትሐዊና ምክንያታዊ በሆነ በጋራ መጠቀም መርህ የአባይን ዉሃ እንደምትጠቀም ለዓለማቀፍ ማህበረሰብና ለግብጽ ህዝብ ማስረዳት ችሏል።

በኢትዮጵያ አነሳሽነት ማንም ሳያስገድድ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ ጥናት እንዲደረግ ዓለማቀፍ የውኃ ባለሙያዎች ቡድን በማዋቀርና በመጨረሻም የባለሙያዎች ቡድን ያቀረበውን ምክረ ሐሳብ ለመተግበር ኢትዮጵያ ተከታታይ የሦስትዮሽ ውይይት በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ብዙ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርጋለች። በዚህም አቋሟ ለግብጽና ሱዳን ህዝብ ትልቅ መተማመኛ መልዕክት ማስተላለፍ ችላለች።

ከመቸዉም ግዜ በላይ ኢትዮጵያ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ከሱዳን ህዝብና ምሁራን ጋር ሰፊ የዉይይት መድረኮችን አድርጋለች። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነዉ በአባይ ዉሃ አጠቃቀም ዙሪያ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራንና

የካይሮ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች  ያደረጉት ሰፊና ዉጤታማ ኮንፈረንስና የኢትዮጵያ አርትስቶች ለአስር ተከታታይ ቀናት በሱዳን በተለያዩ ከተሞች ያሳዩት ባህላዊና ሙዚቃዊ ትርዕት ይጠቀሳል።

የኢትዮጵያ መንግስት የግብጽ ግብዣ ተቀብሎና አክብሮ በግብጽ አዲሱ ፕሬዚዳንት አብዱል ፋታ አል-ሲስ በዓለ ስመት ላይ የሚገኝ በዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም የሚመራ ኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ወደ ካይሮ መላኩና አዲሱ ፕሬዚደንት ከዶ/ር ቴድሮስ ጋር ባደረጉት ዉይይት “ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ታርካዊ ግንኙነት በዉሃ ምክንያት አናበላሽም” ማለታቸዉና ኢትዮጵያ ለመጎበኘት ቃል መግባታቸዉ ለቀጣይ ሶስትዮሽ ድርድር ተስፋ ሰጪና በር ከፋች አካሄድ ነዉ።

የኢፌዲሪ ዉሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በበኩሉ ከፍተኛ የቴክንካልና ፖለቲካል ዉይይቶችን ከግብጽ ጋር በማድረግ ሰፊ የሆነ የማግባባት ስራ ሰርቷል።

ኢትዮጵያ የአባይ ግድብ ጉዳይን በተመለከተ ያደረገችዉ ዲፕሎማሲያዊ ትግል እጅግ በጣም ዉጤታማና ከምን ግዜዉም በላይ ተጨባጭ ዉጤት የተገኘበት ነዉ ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ጉዳይ በቁርጠኝነትና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለመፍታት ተከታታይ ጥረት ብታደርግም ገታራና ተለዋዋጭ በሆነ በግብጽ አቋም ምክንያት ድርድሩ “ዉሃ ቅዳ ዉሃ መልስ” ሆኖ ከቀጠለበት አካሄድ ትንሽ መለስ ያለ ይመስላል። ግብፅ በይፋ ከኢትዮጵያ ጋር በሱዳን ካርቱም በነሃሴ ወር 2006 ለመደራደር ቀጠሮ ይዛለች። የኢትዮጵያ መንግስትም ለዲፕሎማሲያዊ ድርድር ዝግጁ መሆኑን ገልፆል። ምን አዲስ ነገር ይፈጠር ይሆን? አብረን የምናየዉ ይሆናል።

ዘካሪያስ ጣሎ አንጁሎ

Date 15/11/2006

Email zeketalo@yahoo.com